# <u>አለን ባመፅ</u> (ቁጥር ሁለት)

(ከአጅሬው
ዝብርቅርቅ ማህደር)

ካለፈው የቀጠለ

"እብዱ ዘለቀ"

ስናድግ ማለት በልጅነታችን "እብዱ ዘለቀ" እንለው ነበር "እብዱ ዘለቀን"። ስሙ ዘለቀ ይሁን አይሁን እስከዛሬ የማወቀው ነገር የለም። ለምን ዘለቀ የሚለውን ስም እንደመረጥንለት አላስታውስም። ምናልባት ሲራመድና ሲሮጥ አንድ እግሩ አጥሮ አንከስ ስለሚል ይመስለኛል። ስንወለድ እዚያው ሰፈራችን ባይኖር ብቻ ስምንት ዘጠኝ አመት ሲሞላን ጀምሮ እዚያው ሰፈራችን (ሲያምራችሁ ይቅር ሰፈሩን አልናገርም) ነዋሪ ነበር። ቤቱም አዳሩም አንድ የሰፈራችን ትልቅ ሰው የሆኑ አቶ አዳነ የሚባሉ ሰው ቤት ነው። አስጠግተውት ይሆን ወይም ዘመዳቸው የሚያውቅ የለም። ታዲያ "እብዱ ዘለቀን" ስናየው እብዱ ዘለቀ እንለዋለን። አቋራጭ ለአቋራጭ ባቡር መንገድ ለባቡር መንገድ ያባርረናል። የቆመ ኦፔል መኪና ይግጨችሁ፣ የዛፍ ቅጠል ይውደቅባችሁ፣ ቤታችሁ አፈን ከፍቶ ይዋጣችሁ . . .እርግማኑን እንወደዋለን። ያባረራናል እንጂ አይዘንም። እስካስታውስ ድረስ "በእብዱ ዘለቀ የተመታ አንድ ልጅ ብቻ ነው። እርሱንም ድንጋይ ስለወረወረበት እንጅ "እብዱ ዘለቀ ስላለው አልነበረም። አደግንና ትልቅ ጎረምሶች ሆነን "እብዱ ዘለቀን" እብዱ ዘለቀ ማለት ብናቆምም የሰፈራችን ህፃናት የእኛ ትናንሾች በእኛ እግር መተካታቸው አልቀረም።

በጠራራ ፀሐይ በውድቅት ቀን ሰማይ ጠርቶ ብርሃን በደመቀበት ከእለታት አንድ እለት (ካልታደሉት ብዙ እለቶች መካከል በአንዱ እለት) ለጆሮ ቢለመድም ባልተለመለደ ሰአት አንድ የወፍራም ጠመንጃ ፍንዳታ (ተኩስ) ተሰማ። ሠፈር ተደናግጠ። ወላጅ ዛሬ ደግሞ ሳይመሽ ማንን ገደሉ ብሎ ወደ ተኩሱ ተሯሯጠ። እብዱ ዘለቀ በደም ተለውሶ የወደቀውን ወጣት በቁጭታው አቅፎ ኡ ኡ ታዉን አቀለጠው።
"እ ግ ዚ ኦ" . . . "እ ግ ዚ ኦ" . . . "እ ግ ዚ ኦ" . . .
"የሰው ያለህ" . . . "የሰው ያለህ" . . . "ኡ . ኡ . ኡ ."
"ድ ረ ሱ" . . . "ድ ረ ሱ" "እ ር ር ር ር ር ሪ" . . . "አረ ወየው"
"አሳድጌ አሳድጌ ቀጠፉት . . . ቀጠፉት . . . አጫወቼ . . . አጫዋቼ . . . "ሳባርር ሳሮጥ አሳድጌ በእንጭጩ ቀጩት"
"ስንት የሚሰራውን ልጅ!"
ቤተሰቦቹን የሚጠረውን ልጅ"
"ለአገር የሚጠቅመውን ልጅ"
"ባልንጀራየ አሳድጌ አሳድጌ"
"ልጄን አጫዋቼን"
"አገሬ ባለ"
"እምቢየው ባለ" . . . በጠራራ ፀሃይ ቀበሌ ዘበኛ ሌሊት ወረቀት ሲረጭ አይቸዋለሁ ብሎ አድፈጦ ጠብቆ በዝሆን ማደኛ ጠመንጃ ነድሎ የጣለውን ወጣት ደሙ በላዩ ላይ እየተንዠቀዠቀ አንገቱን ታቀፎ ተንሰቀስቆ ማልቀሱን ተያያዘው። ተኩሱንና የ"እብዱ ዘለቀ"ን ጩኸት ሰምቶ የተሰበሰቡት ሰፈረተኞች የራሳቸውን እንባ እያነቡ እብዱ ዘለቀን ከሬሳው አላላቀቁትም። ከዚህ ጊዜ በኋላ የሰፈር ማቲወች "እብዱ ዘለቀን "እብዱ ዘለቀ" ማለት አቆሙ። እብዱ ዘለቀ ለዚህ አቅፎ

ላለቀሰለት ወጣት ቀብር አልተገኘም ነገር ግን ሹልክ እያለ ወጣቱ የተቀበረበት ቤተክርስቲያን በመሄድ ከመቃብሩ ደንጋይ ላይ መቀመጥ ያዘወትር ነበር። ወጣቱ ተመትቶ ወድቆ አቅፎት ሳለ በላዩ ላይ የተንዠቀዠቀውን ደም የጠጣውን ልብሱን አላወልቅ ብሎ ለብዙ ጊዜ ለብሶት ኖረ።

ታዲያ እኔ እንደ እብዱ ዘለቀ ሆኛለሁ። እነኛ ለቁም ነገር ሲታገሉ ደረቅ እውነት ይዘው የወደቁትን ሀቀኛ ታጋዮች አላማ ታጥቄ አላወልቅ እንዳልኩ እነሆ ኢሕአፓ እንደሆንኩ ከሠላሳ አመት በላይ ሆኖኛል። ትፈርዱብኝ ይሆን? የደም ልክፍት እኮ ነው፣ የባልንጀሮቼ የንፁሃኖቹ የደም ልክፍት። በግፍ የተጨፈለቁ አባትና እናቶቼ እነ ዳሮ ነጋሽ እነ መምህር በላይ . . . እህቶቼና ወንድሞቼ እነ ክፍሌ ሻውልና ምስራቅ ማሞ . . .፣ ደም የጠጣችው የምወዳት የአገሬ መሬት ላይ ከተሰዉላት የህዝብ ልጀቿ የተረከበኩት የደም ልክፊት . . . በአላማቸው በወደቁለት በራዕያቸው መፅናት። ዋ እኔስ መታደሌ ከግፍ ጋር ፊት ለፊት እየተያየሁ (ወየውልኝማ ያየኝ ጊዜ። ግን ምኔ ሞኝ ነው የምያዝ ምክንያቱን ባለፈው ፅሁፌ ተናግሬያሁ) ካገሬ ቁጭ ብዬ እታገለዋለሁ። ብሰደድ ኖሮ ምን ይውጠኝ ይሆን። ራሴን ለማስተዋወቅ ለጉድ የጎለተኝ እጅሬው ዘለቅ ይሏል እኔ ነኝ። የማይደፈረውን ሁሉ የተፈራራበትን የኢሕአፓና የኢሕአፓወችን ታሪክ፤ መፃፍ ያለበትን እስከ አሁን ያልተነገረውን ለአገሬ ጨቅላ የማውቀውን ላስረክብ (በየትም ያላችሁ ሙሉበት)። (ስንቶቻችሁ ትሆኑ እብዱ ዘለቀን ሁናችሁ የምትኖሩ?)

ድንገተኛ ግንኙነት

ታሪኬ መጀመሪያ የለውም። አገራችን ኢትዮጵያ ስትፈጠር ተንደርድሮ አሁን ያለበት እድሜ ያለሁበት እድሜ ድረስ የሚቀጥል ነው። እኔ ሳልፍም ይቀጥላል . . .
“አገባህ” አልኩት
“አወ አግብቻለሁ” አለኝ
“ወለድክ” አልኩት
“አወ ሁለት ወልጃለሁ” አለና “አንተስ አለኝ
“እኔ አላገባሁም አልወለድኩም” ስለው እንደመገረም አረገው
“ምነው ለምን?” አለኝ
መልሱን መስጠት ባልፈልግም በድፍረት “የተውከኝ ቦታ ነው ያለሁ” አልኩት
“አልገባኝም አለኝ”
ማብራራት አልፈልግሁም በድፍኑ “እዚሁ አገሬ እንዳለሁ አለሁ” ብየ ቀለድኩ
ለኢሕአፓነት የመለመለኝ ሰውየ ከደርግና ከወያኔ ተርፎ መሃል መርካቶ አገኘሁት። አምሮበታል ነው የሚባለው። ከፈረንጅ አገር (ከአሜሪካ) ለጉብኝት አገሩን ሊያይ ተመልሶ መጥቶ “እከድየ እንዴት አምሮብሃል አንተ አልኩት” መጀመሪያ አላወቅሁትም ነበር። “ደህና ጎረምሳ መስለህ የለም እንዴ” በአነጋገሬ ሳቀልኝ። ተጠምጥሞ ሳመኝ። ከአራት ጊዜ በላይ ፊቴን እያስተዋለ እየመላለሰ አቀፈኝ። ሞቅ ያለ ሰው። ሰው የናፈቀው ሰው። ሰው አይቶ የማያወቅ የሰው ሰው መሰለኝ። ደህና ጉረምሳ መስለሃል ያልኩት የዉነቱን ነበር መኪና መሸከም የሚችል ወጠምሻ መስሎል። “አንተ የአገሬ ገበሬ ብትሆን ጥሩ አራሽ ይወጣህ ነበር” አልኩት። ከልቡ ሳቀና አብሮኝ ቢውል እንደሚወድ ነገር ግን የሚሄድበት ቦታ እንዳለ ነግሮኝ ቀጠሮ ሰጥቶኝ ተለያየን።

የቀጠሮው ቀን እስኪደርስ ቸኮልኩ። መጠንቀቅ እንዳለብኝ አውቃለሁ። ከተዉት ቦታ የሚገኝ የመቃብር ደንጋይ ብቻ ነው። የመቃብር ደንጋይም ዋጋ ካወጣ ከቦታው አይገኝም። በሃሳቤ ብዙ ነገር ሲንሸራሸር ከረመ። ይህን ሰው የተለየሁት ብ1969 (የኛ አቆጣጠር) ዘንድሮ በ1998 ከሃያ ዘጠኝ አመታት በፊት መሆኑ ነው። አሁን የከረረ ፓለቲካ ቢያወራኝ ምን ይሆን የምለው? ፓለቲካ አላውቅም እንዳልለው ፓለቲከኛ ያረገኝ እሱ ነው። ፖለቲካ ትቻለሁ እንዳልለው

አያምነኝም፤ ቢያምነኝስ ደግሞ አይኔን በጨው አጥቤ "ፓለቲካና ኮረንቲ በሩቅ" ማለት እንደማልችልበት አውቃለሁ። ምን አቋም እንደያዝኩ ሳልወስን ቀኖቹ በረሩና የቀጠሮው ቀን ደረሰ። ከቀጠሮው ሰአት በፊት ሰላሳ ደቂቃወች ቀደም ብየ ብደርስም ራቅ ብየ ከባቢውን ሳጤን ቆየሁ (ለምን እንደሁ ባውቅም አላውቅም። አምስት ደቂቃወች አሳልፌ ወደተቀጣጠርንበት ቤት ስገባ ቁጭ ብሎ ሲጠብቀኝ አገኘሁት። በፈገግታ ብድግ ብሎ ሲቀበለኝ

"እንዴት ነው አባሻነትህን አልረሳህም"። አልኩት ቀኝ እጄን ዘርግቼ አጥብቄ እየጨበጥኩት

"እንዴት ይረሳል።" "ቁጭ በል" ሲለኝ ከፊት ለፊቱ ካለው ወንበር ላይ ቁጭ አልኩ።

"ለመሆኑ ጤንነትህ እንዴት ነው?" "ተጎሳቁለሃል ወይንስ እርጅና ነው?" አለ ፊት ፊቴን አተኩሮ እየመለከተ።

"ውስጤ ጎረምሳ ነው። እርጅናው ግን ምን ይጠየቃል" አልኩት

"ዱሮም ቀልደኛ ነበርክ? ብዙ አላስታውሰም" አለኝ ፈገግ እያለ

"ኑሮ ነች ያስተማረችኝ፡ ቀልድ እድሜ ይጨምራል" ስለው ለትንሽ ጊዜ ዝም አለ

"አሁንም ያነበብከውን አትረሳም? ስል ጠየቅሁት ከፈገግታ ጋር

ጥያቄው ድንገተኛ የሆነበት ይመስላል "አትረሳም ነው ያልከው" ብሎ ጥያቄውን ደገመና ዱሮ አልረሳም ነበርኩ እንዴ? ሲል መልሶ ጠየቀኝ

"አይ የነእንትናን መፅሃፎችን(ሶስት አፍ ሁለት ጆሮ) በቃልህ ስትወጣቸው ስትወርዳቸው ስለማስታውስ ነው" አልኩት። በእርግጥም ያነበባቸውን መፅሐፎችን በቃሉ ሲወጣቸው ሲወርዳቸው መፅሐፎቹን የፃፋቸው እርሱ ይመስል ነበር።

ትዝታ ይዞት ትንሽ በረረ አይኑን በሩቅ እንደተከለ "ጥሩ ዘመን ነበር" አለ"። አባባሉ አልገባኝም። ያንን ዘመን እንዴት ጥሩ እንዳለው ልረዳው አልቻልኩም። ግን ደግሞ ምን ማለቱ እንደሆነ አላጓጓኝምና ለምን እንዲህ አልክ ብየ አልጠየቅሁትም።

"ከኛ ጋር ይሰሩ የነበሩ ልጆች ጋር ትገናኛላችሁ? አለኝ ከትንሽ ዝምታ በኋላ። አምስት ሆነን በአንድ ሕዋስ ውስጥ እንሰራ ነበር። በሕይወት የተረፍነው እኔና እርሱ ብቻ መሆናችንን አለማወቁ በጣም አስደነገጠኝ።

እንዴት እንደምነግረው እያሰብኩ "አይ አንገናኝም" አልኩት በደረቁ።

"እስኪ እንፈልጋቸው ለዱሮ ጊዜ ስንል። አምስታችንም አንድ ላይ ቁጭ ብለን እናውጋ" አለ ትዕዛዝ በመሰል አነጋገር። ድንጋጤ ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ ወረረኝ። እንዴት ነው ይህ ሰው ለሃያ ዘጠኝ አመታት ሙሉ አዲስ አበባ ከሁለት አረመኔ ነገሮች፣ ከጠጅና ከኤይድስ ተርፎ ይኖራል ብሎ የሚያስበው እያልኩ ሃዘን እንደ ተጫነኝ፤ ቅሬታየን የተመለከተ ይመስል

"ምን ነው ተሰውተዋል እንዴ?" ብሎ መልሱን ሲመልስልኝ ጭንቱ እንደተራገፈለት አህያ። በሰፊው ተነፍሰኩና አወንታየን በራሴ ንቅናቄ ስገልፅለት ፍዝዝ እንዳለ እንባ በአይኖቹ አቀረሩ።

"ስሜቱ ነበረኝ" ብሎ በዝምታ ተዋጠ። ከራሱ ጋር በውስጡ እያንሾካሸከ እንደሆን በግለፅ ይታይበታል። ከአይኑ የወረዱትን ጥቃቅን የእምባ ዘለላዎች በአይበሉባው አበሰና "ይህን ያህል ዘመን!" "ጊዜው ሮጠ!" "ነገሩ አውቄው ነበር" "አንተን ሳገኝህ ከደስታ ብዛት መስዋዕትነት እንደ ተከፈለ ረሳሁት።" እያለ ስበር ስበር በሚሉ አጫጭር ቃላቶች ንግግሩን ቀጠለ። "እኔ አዲስ አበባን ለቅቄ አመለጥኩ በዚያው ስደት ገባሁ;" "ጊዘውም በዚያው መጠን በረረ።" አለና እንደገና በዝምታ ተዋጠ።

ይህንን ሰው የማውቀው ት/ቤት ነበር (ት/ቤቱን አልናገርም) በሰፈራችንና በእድገታችን አንተዋወቅም። የእኔንም አብረውን የታገሉትንና (በአንድ ህዋስ) የተሰውትን ሶስት ባልደረቦቻንን (ጓዶች እንዳልል ሁሉም ይጠቀምበታል) ሰፈራቸውንና እድገታቸውን አያውቅም። አራታችንንም ወደ ኢሕአፓ ያሰባን እሱ ነው። በዘመኑ ጠንካራ ግለሰብ እንደነበረና ለህዝቡና ለትግሉ ያለው ፍቅር ሃይለኛ እንደነበር አውቃለሁ። ለሰላሳ ጥቂት ፈሪ አመታት መለያየት በኋላ ከፊቴ ቁጭ ብሎ እንባውን በጉንጨቹ ሲያወርድ በማያቴ ምን ስሜት እንደተሰማኝ ልገልፅ ይቸገረኛል። የእኔም

አይኖች እንባ አቀርዝዘው ወደ ፊቴ ሳይወርዱ ውጪ አስቀረሆቸው። ቀጣዩ ጥያቄ ከረር ያለ እንደሚሆን አላጣሁትም። መልሱን በምን መልክ እንደምነግረው ሳስብ
“እንዴት ነው የተሰውት የምታውቀው ነገር አለ?” ብሎ የምጠብቀውን ጥያቄ ጥሬውን ዘረገፈው።
“ታሰረው . . .  ተገርፈው . . . ተሰቃይተው . . . ማንንም አሳልፈው ሳይሰጡ. . . “ አልኩና ዝም አልኩ።
ዝምታየ ስለባዛበት መሰለኝ “ይህ እኮ ታሪካችን ነው መነገር አለበት፣ ማወቅ እፈልጋለሁ”። ለልጆቼም ልጆች ለልጆቼም ይህ ታሪክ እንዲያልፍ የምታወቀውን ብትነገረኝ ደስ ይለኛል።” ሲል ለዛሬ ሌላ ነገር እንጨዋወትና በቀጠሮ ተገናኝተን ሰወር ያለ ስፍራ ቁጭ ብለን የማውቀዉን ሁሉ አጫውትሃለሁ።” እኔም ልዘጋጅበት አንተም ትንሽ እረፍ፤ እንዳየሁህ በጣም ያዘንክ ተመስላለህ።” አልኩት ጠንከር ብየ
“ግንኙታችንም ድንገት ነው ይሁን እሽ” በሚል ተስማምተን ሌላ ሌላ ወግ አወጋንና ከሁለት ቀናት በኋላ ልንገናኝ (የቀጠሮ ቦታችንን አልናገርም) ምሳ ጋብዞኝ ተለያየን (ምሳው እንዴት ጣፈጠኝ መሰላችሁ፤ በአሜሪካን ብር ስለተገዛ መሰለኝ) . . . .  .

ይቀጥላል

አጅሬው ዘብሔረ መርካቶ (ከመርካቶ)